አይርላድ


An Roinn Dlí agus Cirt, Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice, Home Affairs and Migration

EUROPEAN UNION AGENCY FOR ASYLUM

# ስለ ጥገኝነት እና የፍልሰት አስተዳደር ደንብ ማወቅ ያለብዎት ነገር

አይነት ኤ (Type A)

**የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች**




AMHARIC

# ይዘት


ይህን በራሪ ወረቀት ለምን እየተቀበሉ ነው? 3

አለም አቀፍ ጥበቃ ምንድነው ማንስ ነው ማግኘት የሚችለው? 3

የጥገኝነት እና ፍልሰት አስተዳደር ደንብ ምንድነው? 4

ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው? 5

ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለሚሰጠው ውሳኔ እየጠበቁ ሳለ መብቶችዎ 6

ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለሚሰጠው ውሳኔ እየጠበቁ ሳለ የት መቆየት አለብዎት? 8

በዚህ ሂደት ውስጥ ከእርስዎ የሚጠበቀው ምንድን ነው? 8

የትኞቹን ሰነዶች ማሳየት አለብዎት? 9

የጣት አሻራዎን እና ፎቶግራፍዎን ለመስጠት ለምን ግዴታ አለብዎት? 10

ግዴታዎችዎን ካላሟሉ ምን አይነት አሉታዊ ነገር ይከሰታል? 11

እስር ምን ማለት ነው? 12

ባለሥልጣናት ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር እንዴት ይወስናሉ? 13

ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለመረዳት እንዲቻል ቃለ-ምልልስ ሊደረግልዎ ይችላል 16

ቃለ-ምልልስ ሁልጊዜ ይከናወናል? 18

በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ቤተሰብ እንዳለዎት ለማረጋገጥ ምን ማስረጃ ማቅረብ ይችላሉ? 19

ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? 20

በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ ሀገር ውስጥ ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልክተው ከሆነስ? 21

ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ ምን ይከሰታል? 22

ስለ ይግባኝ ሂደት ማወቅ ያለብዎት (የእግድ ተፈጻሚነት እና ቀጣይ ይግባኝ ሲለያዩ) 24

ምን ዓይነት የግል መረጃ ይሰበሰባል? 25

ከግል መረጃዎ ጋር በተያያዘ ያሉዎት መብቶችዎ ምንድናቸው? 25

## ይህን በራሪ ወረቀት ለምን እየተቀበሉ ነው?

በ31 የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች በአንደኛው ዓለም አቀፍ ጥበቃ (ጥገኝነት በመባልም ይታወቃል) ጠይቀዋል። ይህ ማለት እርስዎ አሁን ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ነዎት ማለት ነው። ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ሊኖረው ይችላል። አሁን ለዚያ ውሳኔ እየጠበቁ ነው።

ይህ የትኛው አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል፣ የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች እንዴት እንደሚተባበሩ መረዳት አስፈላጊ ነው።

ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ያገኛሉ።

## አለም አቀፍ ጥበቃ ምንድነው ማንስ ነው ማግኘት የሚችለው?



ስደትን ወይም ጥቃትን በመፍራት ወይም ከባድ ጉዳት የመድረስ አደጋ ስላጋጠምዎት ወደ ሀገርዎ መመለስ ካልቻሉ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ሊያስፈልግዎ ይችላል። ይህ ማለት ለምሳሌ ሕይወትዎ ወይም ነፃነትዎ አደጋ ላይ ይሆናል ማለት ነው እና የአገርዎ ባለስልጣናት ከሚገጥሙት አደጋ አይጠብቁዎትም ማለት ነው።

ስለ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ተጨማሪ መረጃ በተለየ በራሪ ወረቀት ውስጥ ያገኛሉ።

**አሁን በ አይርላድ ውስጥ ነዎት፣ እሱም የአውሮፓ ህብረት+ አገር ነው።**
**የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች የሚከተሉት ናቸው:**

27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት:- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና

4 ሌሎች ሀገራት:- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ።

## የጥገኝነት እና ፍልሰት አስተዳደር ደንብ ምንድነው?




የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች የጥገኝነት እና ፍልሰት አስተዳደር ደንብ (Asylum and Migration Management Regulation፣ AMMR) የሚባል የጋራ ሕግ ላይ ተስማምተዋል። ይህ ሕግ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻን የመመርመር ኃላፊነት ያለው የትኛው አገር እንደሆነ ለመወሰን ይረዳል። ይህ ሕግ አንድ አገር በአንድ ጊዜ ከመጠን በላይ ማመልከቻዎች ከደረሱበት፣ የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ያስችላል።

ከአውሮፓ ህብረት+ አገሮች አንዱ ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ዋስትና ይሰጥዎታል፣ ነገር ግን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ኃላፊነት እንደሚወስድ መምረጥ አይችሉም። ማመልከቻዎን የሚመረምረው አገር የሚወሰነው በAMMR ሕግ ደንቦች ነው።

በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ያልገባዎት ነገር ካለ፣ የኢሚግሬሽን መኮንን መጠየቅ ይችላሉ።



በዚህ ጊዜ፣ የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለው የትኛው እንደሆነ ብቻ ነው የሚወስኑት።

ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ከተወሰነ፣ ወደዚያ አገር ይዘዋወራሉ።

## ዝውውር ማለት ምን ማለት ነው?



የአውሮፓ አገሮች እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበት አንዱ መንገድ የሚከተሉትን ኃላፊነት በመውሰድ ነው:-

- በአሁኑ ጊዜ በሌላ የአውሮፓ አገር ውስጥ የሚኖሩ አመልካቾች
- በቅርብ ጊዜ በሌላ የአውሮፓ አገር ዓለም አቀፍ ጥበቃ የተሰጣቸው ሰዎች።

ይህ ዝውውር (relocation) በመባል ይታወቃል።

ለዝውውር ግምት ውስጥ ገብተው ከሆነ፣ '**ስለ ዝውውር ማወቅ ያለብዎት**' በሚል ርዕስ የትኞቹ የአውሮፓ አገሮች በዝውውር ውስጥ እንደሚሳተፉ ጨምሮ ስለዚህ ሂደት የበለጠ መረጃ የያዘ በራሪ ወረቀት ይደርስዎታል።

**አስፈላጊ!** ለዝውውር ከተመረጡ፣ ወደ የትኛው አገር እንደሚዘዋወሩ መምረጥ አይችሉም።

## ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለሚሰጠው ውሳኔ እየጠበቁ ሳለ የሚኖርዎት መብቶች



ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ነፃ **የሕግ ምክር** የማግኘት መብት አለዎት። ይህንን በማንኛውም ጊዜ ከባለሥልጣናት መጠየቅ ይችላሉ።

የሕግ አማካሪው ስለ መብቶችዎ ያሳውቅዎታል እና በሂደቱ ወቅት ይደግፍዎታል። ጠበቃ ለመቅጠር አስቀድመው ከከፈሉ፣ ባለሥልጣናት ነፃ የሕግ ምክር ላይሰጡዎት ይችላሉ። የሕግ ምክር በቡድን ሁኔታ ውስጥ ሊሰጥ ይችላል፣ ነገር ግን አማካሪው የግል መረጃዎን ከሌሎች ሰዎች ጋር አያጋራም።

የሕግ አማካሪ ለመጠየቅ ባለሥልጣናትን በሚከተለው ማግኘት ይችላሉ:- **በሲቲዌስት የመቀበያ ማዕከል በሊግ ኤይድ ቦርድ የሲቲዌስት የምክር አገልግሎት መረጃ እና የህግ ምክር መጠየቅ ይችላሉ።**



ስለ ሁኔታዎ ማውራት ቀላል እንዲሆንልዎ ከፈለጉ ወንድ ወይም ሴት አስተርጓሚ እና ጉዳይ ተቆጣጣሪ መጠየቅ ይችላሉ። ባለሥልጣናት በሚቻልበት ቦታ ፍላጎቶችዎን ያከብራሉ።



የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር የሚወስነውን ሂደት የዘመነ መረጃ የመጠየቅ መብትም አለዎት። የዘመነ መረጃ መጠየቅ ከፈለጉ፣ ባለሥልጣናትን ወደ contact@ipo.gov.ie ኢሜይል በመላክ።




በጥገኝነት ሂደት በማንኛውም ደረጃ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኤጀንሲ (United Nations Refugee Agency፣ UNHCR) ጋር የመገናኘት እና የመነጋገር መብት አለዎት።

UNHCR የጥገኝነት ጠያቂዎችን እና ስደተኞችን ጥቅም እና መብቶችን ይጠብቃል።

የUNHCR አድራሻ ዝርዝሮች እና የጥገኝነት አሰራር መረጃ በUNHCR  ድረ-ገጽ በ https://help.unhcr.org/ ላይ ይገኛሉ።

**ስለሚቀበሉት ድጋፍ እና አገልግሎት ተጨማሪ መረጃ በተለየ በራሪ ወረቀት ማግኘት ይችላሉ።**

## ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለሚሰጠው ውሳኔ እየጠበቁ ሳለ የት መቆየት አለብዎት?



- ለጊዜው በዚህ አገር ውስጥ መቆየት ግዴታዎ ነው፡፡
- ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር መሄድ የሚችሉት በባለስልጣናት ፈቃድ ከተሰጠዎት ብቻ ነው፡፡
- ባለሥልጣናት ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን መመርመር አለበት ብለው ከወሰኑ፣ ባለሥልጣናቱ ወደዚያ አገር ጉዞዎን ያዘጋጃሉ፡፡

## በዚህ ሂደት ውስጥ ከእርስዎ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡-

- ማመልከቻዎ እየተመዘገበ ባለበት ጊዜ በዚህ አገር ውስጥ ይቆዩ፡፡
- ከዚህ በፊት ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ተሰጥቶዎት ከሆነ፣ እዚያ እንደደረሱ ፈቃዱን ወደሰጠዎት አገር ጥገኝነት ይጠይቁ፡፡
- ማንነትዎን ለማረጋገጥ ያሉዎትን መታወቂያ ሰነዶች በሙሉ ያቅርቡ፡፡
  መታወቂያ ሰነድ ከነበረዎት ግን አሁን ከእርስዎ ጋር ከሌለ፣ ካሁን በፊት በአገርዎ መንግሥት ተሰጥተዎት እንደነበር አሁንም ለባለሥልጣናት መንገር አለብዎት፡፡
- ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር የተጓዙበትን ማንኛውንም ጊዜ ለባለሥልጣናት ያሳውቁ፡፡
- በአውሮፓ ህብረት+ አገር ያለፈቃድ ከቆዩ ለባለሥልጣናት ያሳውቁ፡፡
- በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ያሉዎትን ቅርብ ቤተሰብ በተመለከተ ለባለሥልጣናት ያሳውቁ፡፡

**አስፈላጊ!** በሕግ የጣት አሻራዎን እንዲሰጡ እና ፎቶግራፍዎ እንዲወሰድ ግዴታ አለብዎት፡፡

## የትኞቹን ሰነዶች ማሳየት አለብዎት?

ከእርስዎ ጋር ያሉትን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚመለከቱ ሁሉንም ሰነዶች ለባለሥልጣናት ያካፍሉ፡-




- የእርስዎ የማንነት ማረጋገጫ (የልደት የምስክር ወረቀት፣ ፓስፖርት፣ መታወቂያ ካርድ)



- በአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ውስጥ ያሉ ቅርብ የቤተሰብ አባላት (ኦፊሴላዊ ሰነዶች፣ እንደተምትነጋገሩ የሚያሳይ ማስረጃ)




- በአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ውስጥ ከዚህ በፊት ስለቆዩባቸው ጊዜያት (በመኖሪያ ፈቃድ፣ በቪዛ ላይ የተመሠረተ ወይም የትምህርት ቤት ወይም የዩኒቨርሲቲ ዲፕሎማ ለማግኘት)።

ይህን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ያቅርቡ። በዚህ መንገድ፣ ለማመልከቻዎ ኃላፊነት ያለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር በፍጥነት ሊታወቅ ይችላል።

## የጣት አሻራዎን እና ፎቶግራፍዎን መስጠት ለምን ግዴታ ሆነ?



በዚህ አገር ያሉ ባለሥልጣናት የጣት አሻራዎን እና ፎቶግራፍዎን ይወስዳሉ። ይህ መረጃ፣ ከየማንነትዎ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው መረጃዎች ጋር፣ ዩሮዳክ (Eurodac) ወደሚባል የጋራ የአውሮፓ የመረጃ ቋት ይተላለፋል።

ይህ የመረጃ ቋት በሁሉም መረጃዎን ማየት በሚችሉ 31 የአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ያለፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ከተዘዋወሩ እና የጣት አሻራዎ እንደገና ከተወሰደ፣ በዩሮዳክ (Eurodac) ውስጥ የተከማቸ ሁሉም መረጃዎ በዚያ አገር ባለሥልጣናት ይታያል።

ስለ ዩሮዳክ የመረጃ ቋት ተጨማሪ መረጃ በተለየ በራሪ ወረቀት ቀርቧል።




## ግዴታዎችዎን ካላሟሉ ምን አይነት አሉታዊ ነገር ይከሰታል?



ከባለሥልጣናት ጋር ካልተባበሩ፣ ይህ በማመልከቻዎ ላይ አሉታዊ ውጤቶች ይኖረዋል።

የጣት አሻራዎን ካልሰጡ፣ ባለሥልጣናት በአውሮፓ ውስጥ ለጥገኝነት ፍላጎት እንደሌለዎት ሊወስኑ ይችላሉ። ማመልከቻዎን መመርመር ያቆማሉ፣ ይህም ማለት በዚያ አገር ውስጥ የመቆየት መብትዎ ያበቃል ማለት ነው።

ያለፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ከተጓዙ ወይም በተለየ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ዓለም አቀፍ ጥበቃ ከጠየቁ፣ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወዳለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ሊመለሱ ይችላሉ።




ከሚፈለግበት አገር ውጭ በሆነ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ከሆኑ፣ ነፃነትዎ ሊገደብ ይችላል እና አነስተኛ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ።

## እስር ማለት ምን ማለት ነው?

እስር ማለት በነፃነት መውጣት በማይችሉበት በተወሰነ ስፍራ መቀመጥ ማለት ነው። ባለሥልጣናት እርስዎን ለማሰር ትክክለኛ ምክንያት ሊኖራቸው ይገባል። በእርስዎ ጉዳይ ሌላ አማራጭ እንደሌለ እርግጠኛ መሆን አለባቸው። ውሳኔ ከማድረጋቸው በፊት ባለሥልጣናት የእርስዎን ግላዊ ሁኔታ ይገመግማሉ። የመታሰር ምክንያቶች ለምሳሌ:-



- የጥገኝነት ማመልከቻዎ አስፈላጊ ገጽታዎች (ለምሳሌ የእርስዎ ማንነት) ያለእስር ማረጋገጥ ካልተቻለ
- በተወሰነ ቦታ የመቆየት ግዴታዎን ካላከበሩ፣ ወይም እንደገና የመሸሽ እና ባለሥልጣናት እርስዎን ማግኘት የማይችሉበት ስጋት ካለ
- የጥገኝነት ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወደሚኖርበት የአውሮፓ ህብረት+ አገር የመዛወር ውሳኔ ከተቀበሉ እና ከመዛወርዎ በፊት የመሸሽ ስጋት ካለ
- የደኅንነት ስጋት ከፈጠሩ።

ከታሰሩ፣ ውሳኔውን መቃወም (ይግባኝ ማለት) እና ነፃ የሕግ ድጋፍ እና ውክልና መጠየቅ ይችላሉ።

❗ **አስፈላጊ !** ያለፈቃድ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ከተጓዙ፣ ወደፊት የመታሰር እድልዎ ይጨምራል።

## ባለሥልጣናት ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር እንዴት ይወስናሉ?

በአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ሲያመለክቱት ይህ የመጀመሪያዎ ከሆነ፣ አንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ።

### 1) የቤተሰብ ትስስር



የመጀመሪያው እና በጣም አስፈላጊው ምክንያት በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ዓለም አቀፍ ጥበቃ የተሰጠው ወይም በአሁኑ ጊዜ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ እየጠየቀ ያለ ቅርብ የቤተሰብ አባል ካለ ነው፤ እና የእርስዎ ማመልከቻ ከመመርመሩ በፊት ከእነሱ ጋር እንዲገናኙ መደረግ አለብዎት።

ቅርብ የቤተሰብ አባላት ተብለው የሚታሰቡት:-

- ባለቤትሽ ወይም ሚስትህ
- የተረጋጋ ግንኙነት ያለዎት ግን ያላገቡት አጋርዎ
- ልጅዎ (ከ18 ዓመት በታች እና ያላገባ) ናቸው።

**አስፈላጊ!** ወደ አውሮፓ ህብረት+ አገሮች ክልል ከመግባታዎ በፊት ከዚያ ሰው ጋር ግንኙነት እንደነበርዎት በተቻለ ፍጥነት ማረጋገጥ መቻል አለብዎት። ይህ ጊዜ ከትውልድ አገርዎ የተጓዙበትን ጉዞ ሊያካትት ይችላል።

በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር የሚኖር የቤተሰብ አባል ካለዎት፣ መረጃ ለማቅረብ በጣም ጥሩው መንገድ '**የቤተሰብ ፍለጋ ቅጽ**' የሚባለውን ቅጽ በመሙላት ነው። በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር የሚኖር የቤተሰብ አባል ካለዎት እና ይህን ቅጽ ገና ካልተቀበሉ፣ ከመኮንን ወይም ከሕግ አማካሪዎ ጋር ይነጋገሩ። ቅጹን ለመሙላትም ሊረዱዎት ይችላሉ።

ስለ ከቤተሰብ አባላት ጋር የመገናኘት ዕድል የበለጠ ዝርዝር መረጃ '**በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ቤተሰብ እንዳለዎት ለማረጋገጥ ምን ማስረጃ ማቅረብ ይችላሉ?**' በሚለው ክፍል ውስጥ ማግኘት ይችላሉ።

## 2) ወደ አንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ለመግባት ፈቃድ

አንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ሊወስድ ይችላል፣ የሚከተለው ከሆነ፡-




- የአንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ካለዎት።
- አገር ቤትዎ ከዚያ አገር ጋር ስምምነት ስላለው ያለ ቪዛ እንዲገቡ በተፈቀደልዎ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ከገቡ።

## 3) የትምህርት ማረጋገጫ ወይም ዲፕሎማ



- በአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ በሚገኝ የትምህርት ተቋም ውስጥ ቢያንስ ለአንድ አካዳሚያዊ ዓመት በአካል ከተማሩ በኋላ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት ወይም ዲፕሎማ ከተሰጠዎት።

## 4) ወደ አንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር በሕገ-ወጥ መንገድ መግባት

ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ሊወስድ ይችላል፣ የሚከተለው ከሆነ፡-



- ከአውሮፓ ህብረት+ አገሮች አንዱን የውጭ ድንበር ያለፈቃድ ከተሻገሩ



- ወደ አውሮፓ በሚጓዙበት ጊዜ በአውሮፓ ህብረት+ አገር ባለሥልጣናት በባህር ላይ ከሞት ከዳኑ።



- በአውሮፓ ህብረት+ አገሮች ውስጥ ባሉ አውሮፕላን ማረፊያዎች የመሸጋገሪያ ዞን (transit zone) ውስጥ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካቀረቡ።

## 5) ተንከባካቢ እና ጥገኛ የቤተሰብ አባላትን ማገናኘት

በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ባለው የቤተሰብ አባል እንክብካቤ ላይ ጥገኛ ከሆኑ ወይም በአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ በእርስዎ እንክብካቤ ላይ ጥገኛ የሆነ የቤተሰብ አባል ካለዎት።



ጥገኛ የሆነው የቤተሰብ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች እርዳታ ሊፈልግ ይችላል፦

- እርግዝና
- አዲስ የተወለደ ልጅ መኖር
- ከባድ የአእምሮ ወይም የአካል ሕመም
- ከባድ የአካል ጉዳት
- ከባድ የስነ ልቦና ጉዳት
- እርጅና።

አንዳችሁ በሌላኛው ጥገኛ በሚሆንበት ሁኔታ፣ እርስዎ ጥገኛ የሆነውን ሰው መንከባከብ እንደሚችሉ ወይም የቤተሰብዎ አባል እርስዎን መንከባከብ እንደሚችል ማሳየት መቻል አለብዎት።

## 6) ሰብአዊ ምክንያቶች

አንድ የተወሰነ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን ሊመረምር የሚችልበት ሰብአዊ ምክንያት ሊኖር ይችላል። ይህ በሚከተሉት መሠረት ሊሆን ይችላል፦

- የቤተሰብ ጉዳዮች
- ማህበራዊ ጉዳዮች
- ባህላዊ ጉዳዮች።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንዲመረምር ሊጠየቅ ይችላል፣ ነገር ግን የመጨረሻው ውሳኔ የሚወሰነው በዚያ አገር ውስጥ ባለው ባለሥልጣን ነው።

## ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለመረዳት እንዲቻል ቃለ-ምልልስ ሊደረግልዎ ይችላል

ለጥገኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ባለሥልጣናት የግል ቃለ-ምልልስ ማዘጋጀት አለባቸው።

**አስፈላጊ!** ይህ የጥገኝነት ቃለ-ምልልስ አይሆንም። ቃለ-ምልልሱ ማመልከቻዎን የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚመረምር ለመወሰን ያለመ ነው።

**ይህ ቃለ-ምልልስ አራት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡-**

- ኃላፊነት ያለበትን የአውሮፓ ህብረት+ አገር ለመወሰን ባለሥልጣናትን የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ
- ኃላፊነት ያለበትን የአውሮፓ ህብረት+ አገር የሚወስነው ሂደት እንዴት እንደሚከናወን ማንኛውም ጥያቄ እንዲጠይቁ ለመፍቀድ
- ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር መዘዋወር እንደሌለብዎት ወይም በዚህ አገር እንዲቆዩ መፈቀድ እንዳለብዎት የሚያብራራ ማንኛውም ምክንያቶች ካሉዎት ለመጠየቅ።

ቃለ-ምልልሱ በጥሩ ሁኔታ በሚረዱት ቋንቋ ይካሄዳል። እንግሊዝኛ የማትናገሩ ከሆነ፣ በቃለ መጠይቁ ወቅት ከባለስልጣናት ጋር እንድትገናኙ አስተርጓሚ ይረዳዎታል።



የሚሰጡት መረጃ ሁሉ ከትውልድ አገርዎ መንግሥት ወይም ባለሥልጣናት ጋር አይጋራም።

በቃለ-ምልልሱ ወቅት ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይችላሉ። ሁሉንም ነገር መረዳት ለእርስዎም ሆነ ለመኮንኑ አስፈላጊ ነው፣ ስለዚህ ጥያቄዎች መጠየቅ ሁልጊዜም ተቀባይነት አለው።



የቃለ-ምልልሱ ድምፅ ይቀዳል እና የተነገረው ነገር የጽሑፍ ማጠቃለያ እንዲያዩት ይደረጋል።

የግል ቃለ-ምልልስዎን የጽሑፍ ማጠቃለያ ከተቀበሉ በኋላ፣ ማንኛውም መረጃ ትክክል አይደለም ብለው ካሰቡ እና ማስተካከል ከፈለጉ፣ ማንኛውንም ስህተት ለማረም እና ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ እድሉ ይኖርዎታል።

አስፈላጊ ከሆነ፣ ከቃለ-ምልልሱ በኋላ ተጨማሪ ሰነዶችን አሁንም ማቅረብ ወይም ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር መዘዋወር የሌለብዎትን ምክንያቶች መስጠት ይችላሉ።

እስካሁን ያላቀረቡት መረጃ ወይም ሰነዶች ካሉዎት፣ ለባለሥልጣናት ማቅረብ አለብዎት።

በአለም አቀፍ የጥበቃ ፖርታል ላይ ወደ ኤሌክትሮኒክ አካውንትዎ ማስገባት ወይም በኢሜል ወደ contact@ipo.gov.ie ማስገባት ይችላሉ።

## ቃለ-ምልልስ ሁልጊዜ ይከናወናል?

ለጥገኝነት የመጀመሪያ ጊዜዎ የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ባለሥልጣናት የግል ቃለ-ምልልስ ሳያደርጉ ውሳኔ ሊሰጡ ይችላሉ፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሉ፡-

- ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር አስቀድሞ የሚታወቅ ከሆነ።
- ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለው የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሆነ ለመወሰን አስቀድሞ በቂ መረጃ ካላቸው።
- ለምን መገኘት እንዳልቻሉ ለባለሥልጣናት ሳይናገሩ ከዚህ ቀደም ቃለ-ምልልስ ካመለጠዎት።
- ከባለሥልጣናት ጋር መገናኘት ካልቻሉ።

ቃለ-ምልልስ ካልተዘጋጀ፣ እንዲዘጋጅሎት መጠየቅ ይችላሉ። መኮንኖቹ ጉዳይዎን ለመያዝ በቂ መረጃ አለን ብለው ካሰቡ፣ ይህን ጥያቄ ሊከለክሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን ቃለ-ምልልስ ያለማድረጋቸውን ምክንያት ማቅረብ አለባቸው።

ቃለ መጠይቅ ካልተደራጀ፣ አንዱን መጠየቅ ይችላሉ። መኮንኖቹ ጉዳይዎን ለማስተናገድ የሚያስችል በቂ መረጃ እንዳላቸው ካሰቡ፣ ይህንን ጥያቄ ውድቅ ሊያደርጉት ይችላሉ ነገር ግን ቃለ መጠይቁን ላለማድረግ የወሰኑበትን ምክንያት ማቅረብ አለባቸው።

## በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ቤተሰብ እንዳለዎት ለማረጋገጥ ምን ማስረጃ ማቅረብ ይችላሉ?

ስለ ቤተሰብ አባልዎ መረጃ ለማቅረብ በጣም ጥሩው መንገድ '**የቤተሰብ ፍለጋ ቅጽ**' የሚባለውን ቅጽ በመሙላት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ግንኙነታችሁን ማረጋገጥ የሚችሉ ማናቸውንም ኦፊሴላዊ የመንግሥት ሰነዶች ያቅርቡ። ሌሎች የማስረጃ ዓይነቶች ማቅረብም ይችላሉ፣ ለምሳሌ ከቤተሰብ አባልዎ ጋር ሲነጋገሩ እንደቆዩ የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንደ ፎቶዎች፣ ኢሜይሎች ወይም የጽሑፍ መልእክቶች።



ስለ ግንኙነታችሁ ምንም አይነት ማስረጃ ከሌልዎት፣ ባለሥልጣናት ዝምድና እንዳለባችሁ ለማረጋገጥ የዲኤንኤ ምርመራ እንዲያደርጉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ።

በጽሑፍ መገናኘት እንደምትፈልጉ ሁለታችሁም ከገለጻችሁ ብቻ ከቤተሰብ አባልዎ ጋር መገናኘት ትችላላችሁ። ይህንን ሰነድ ከቻሉ በእንግሊዝኛ ለማቅረብ መሞከር አለብዎት።

ይህን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ማዘጋጀት ይጀምሩ።



ስለ ቤተሰብ የመገናኘት ወይም ውህደት ሂደት ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ምክር ከፈለጉ፣ ከሕግ አማካሪ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር የቤተሰብ አባል ካለዎት ግን ግንኙነታቹ ተቋርጦ ከሆነ፣ እነሱን ለማግኘት ሊረዱዎት የሚችሉ ድርጅቶች አሉ።

እነዚህን ድርጅቶች ከዚህ በታች ያለውን መረጃ በመጠቀም ማግኘት ይችላሉ፡-
የአየርላንድ ቀይ መስቀል ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች የተለያዩ ድጋፎችን ይሰጣል። ስለ ቤተሰብ ፍለጋ መረጃ ለማግኘት Find Missing Family - Irish Red Cross ን ይመልከቱ።

## ሂደቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?



በአገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በተለምዶ **ከ1 ወር ተኩል** እስከ **3 ወራት** ይወስዳል፣ ነገር ግን ይህ እንደ ጉዳይዎ ሁኔታ **ረዘም ሊል ይችላል።**



ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ካረጋገጠ፣ እርስዎን የማዛወር ጥያቄውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ **በ6 ወራት ውስጥ** ይዛወራሉ።





ጥያቄው በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር የቤተሰብ አባል ስላለዎት ከሆነ፣ ዝውውሩ **ቅድሚያ ይሰጠዋል።**



በአሁኑ ጊዜ **ከታሰሩ ወይም ለወደፊቱ ከታሰሩ**፣ ጉዳይዎ **በአስቸኳይ ይታያል**። ዝውውርዎ **በ5 ሳምንታት** ውስጥ መመቻቸት አለበት። ዝውውሩ በ5 ሳምንታት ውስጥ ካልተከናወነ፣ ከእስር ይፈታሉ። ሆኖም፣ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ከተቀበለበት ቀን አንስቶ **በ6 ወራት ውስጥ** አሁንም ዝውውርዎን ይዘጋጃል።

ወንጀል በመፈጸምዎ ምክንያት በእስር ላይ ከሆኑ፣ የዝውውሩ የጊዜ ገደብ **እስከ 1 ዓመት ሊጨምር ይችላል።**




**አስፈላጊ!** ከሸሹ፣ ከተደበቁ ወይም በዝውውሩ አደረጃጀት ላይ ከባለሥልጣናት ጋር ካልተባበሩ፣ **ለዝውውሩ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እስከ ከፍተኛው 3 ዓመት ሊራዘም ይችላል።**

## በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ ሀገር ውስጥ ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልክተው ከሆነስ?

ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት የሚፈቀድልዎ በአንድ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ብቻ ነው። በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ አስቀድመው ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልክተው ከሆነ፣ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወዳለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ይመለሳሉ።

ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት የሚያሳይ መረጃ ካለ፣ ለዚያ አገር ማሳወቂያ ይላካል። ያ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ካረጋገጠ፣ ወደ የትኛው የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንደሚዘዋወሩ የሚገልጽ **የዝውውር ውሳኔ** ይሰጥዎታል።

ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚያመለክቱበት ይህ የመጀመሪያ ጊዜዎ ካልሆነ፣ ወይም ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት አስቀድሞ ከተወሰነ፣ ባለሥልጣናት ከእርስዎ ጋር የግል ቃለ-ምልልስ ላያደርጉ ይችላሉ።

ሆኖም፣ ለምን ወደዚያ አገር መዘዋወር እንደሌለብዎት ወይም ለምን በዚህ አገር እንዲቆዩ ሊፈቀድልዎት እንዳለበት ለማስረዳት ዕድል ይኖርዎታል።

ይህን መረጃ እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ መረጃ ከዚህ በታች ማግኘት ይችላሉ፡-
**ይህንን መረጃ በአለም አቀፍ ጥበቃ ፖርታል ላይ ባለው የኤሌክትሮኒክ አካውንትዎ ወይም በኢሜል ወደ contact@ipo.gov.ie ማቅረብ ይችላሉ።**

## ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ ምን ይከሰታል?

ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር እንዲዘዋወሩ የዝውውር ውሳኔ ከደረሰዎ፣ አንዳንድ መብቶችዎ ይሰረዛሉ፣ ለምሳሌ:-

- **በርካታ የድጋፍ ዓይነቶች እና አገልግሎቶችን አያገኙም።**
- **ስራ እንዲሠሩ** ወይም **ኮርሶችን እንዲከታተሉ አይፈቀድልዎትም።**





ዝውውሩ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ካረጋገጠ ወይም ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ6 ወራት ውስጥ መከናወን አለበት።

ከታሰሩ፣ ጉዳይዎ በአስቸኳይ ይያዛል። ዝውውርዎ በ5 ሳምንታት ውስጥ መመቻቸት አለበት። ዝውውሩ በ5 ሳምንታት ውስጥ ካልተከናወነ፣ ከእስር ይፈታሉ።

ዝውውርዎ አሁንም የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን እንደሚመረምር ካረጋገጠበት ወይም ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ ይዘጋጃል።

ወንጀል በመፈጸምዎ ምክንያት በእስር ላይ ከሆኑ፣ የዝውውሩ የጊዜ ገደብ እስከ 1 ዓመት ሊጨምር ይችላል።

**አስፈላጊ!** ከሸሹ ወይም ከባለሥልጣናት ጋር ካልተባበሩ፣ **ለዝውውሩ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እስከ ከፍተኛው 3 ዓመት ሊጨምር ይችላል።**

## የዝውውር ውሳኔውን ካልተቀበሉ ምን ይከሰታል?



ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ከተወሰነ፣ **የዝውውር ውሳኔ** ይደርስዎታል። ይህ ውሳኔ ወደ የትኛው አገር እንደሚዘዋወሩ ያሳውቅዎታል።

በዝውውር ውሳኔው ካልተስማሙ፣ ምክንያቶችዎን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ይግባኝ ማቅረብ ይባላል። ውሳኔውን ይግባኝ ሲሉ፣ ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ሰጪ አካል የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል።

የዝውውር ውሳኔን ለመቃወም (ይግባኝ ለማለት) ሦስት ምክንያቶች ብቻ አሉ፡-

- ወደዚያ የተወሰነ የአውሮፓ ህብረት+ አገር መዘዋወርዎ የሰብአዊ መብቶችዎን ይቃረናል ብለው ከተከራከሩ።
- በዝውውሩ ውሳኔ ጊዜ ያልነበረ ነገር ግን ውሳኔውን ሊለውጠው የሚችል አዲስ መረጃ ሲኖር።
- በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ቤተሰብ ካለዎት እና በምትኩ ከእነሱ ጋር መገናኘት ካለብዎት።

የራስዎን የሕግ አማካሪ ለመቅጠር አቅም ከሌለዎት፣ ነፃ የሕግ አማካሪ ይግባኙ ላይ እንዲረዱዎት ይቀርብልዎታል።




በዚህ ሂደት በሙሉ እርስዎ ሊረዱት የሚችሉትን ቋንቋ የሚናገር አስተርጓሚ ይደግፍዎታል።

## ስለ ይግባኝ ሂደት ማወቅ ያለብዎት፣ የእግድ ተፈጻሚነት እና ቀጣይ ይግባኝ የተለያዩ ሲሆኑ

የዝውውር ውሳኔው በሚሰጥዎ ጊዜ ይግባኝ ለማቅረብ ያለው የጊዜ ገደብ፣ የት እና እንዴት እንደሚሆን ይብራራል።

ለመጀመር፣ ይግባኝዎ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ በዚህ አገር ውስጥ እንዲቆዩ መፈቀድ ያለብዎትን ምክንያት(ዎች) እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። **ይህ** የእግድ ተፈጻሚነትን ይግባኝ በመባል ይታወቃል።

ፍርድ ቤቱ ይግባኝዎ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ በዚህ አገር ውስጥ እንዲቆዩ መፈቀድ እንዳለብዎት ወይም እንደሌለብዎት **በ1 ወር** ጊዜ ውስጥ ይወስናል።

ፍርድ ቤቱ ይግባኝዎ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ በዚህ አገር ውስጥ እንዲቆዩ መፈቀድ የለበትም ብሎ ከወሰነ፣ ይግባኝዎ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወዳለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ይዘዋወራሉ።

ፍርድ ቤቱ ይግባኝዎ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ በዚህ አገር ውስጥ እንዲቆዩ መፈቀድ እንዳለበት ከወሰነ፣ ከዚያም ከዝውውር ውሳኔው ጋር የማይስማሙበትን ምክንያት(ዎች) እንዲያቀርቡ ይጠይቅዎታል። ፍርድ ቤቱ ከዚያ በኋላ የእግድ ተፈጻሚነት ይግባኝ ከወሰነበት ጊዜ አንስቶ **በ1 ወር** ውስጥ ውሳኔ ሊሰጥዎ ይሞክራል።

ይግባኝዎ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ወዳለው የአውሮፓ ህብረት+ አገር ይዘዋወራሉ። ዝውውሩ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ6 ወራት ውስጥ መከናወን አለበት።

በአሁኑ ጊዜ ከታሰሩ ወይም ለወደፊቱ ከታሰሩ፣ ጉዳይዎ በአስቸኳይ ይታያል። ዝውውርዎ በ5 ሳምንታት ውስጥ መመቻቸት አለበት። ዝውውሩ በ5 ሳምንታት ውስጥ ካልተከናወነ፣ ከእስር ይፈታሉ። ሆኖም፣ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ6 ወራት ውስጥ አሁንም ዝውውርዎን ይዘጋጃል።

**አስፈላጊ!** ሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ካለበት ከባለሥልጣናት ጋር መተባበር አለብዎት።

## ምን ዓይነት የግል መረጃ ይሰበሰባል?



እርስዎ በሚቆዩበት የአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ያሉ መኮንኖች የሚከተሉትን ጨምሮ የተወሰኑ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፦

- የእርስዎ የግል ዝርዝሮች እና ከእርስዎ ጋር የሚጓዙ የቤተሰብ አባላት (ስም፣ ዜግነት፣ የትውልድ ቀን እና ቦታ)። ቀደም ሲል የተለያዩ ስሞችንና ዝርዝሮችን ከተጠቀሙ፣ ስለዚያ ይጠይቁዎታል።
- ስለ ማንነትዎ እና የጉዞ ሰነዶችዎ መረጃ።
- ማንነትዎን ሊያረጋግጥ የሚችል ማንኛውም ሌላ መረጃ፣ ለምሳሌ የጣት አሻራዎ።
- በሌላ የአውሮፓ ህብረት+ አገር ስለሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ዝርዝሮች፣ ለምሳሌ የግል ዝርዝሮቻቸው፣ ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙበት ጊዜ፣ ያሉበት ቦታ እና ሕጋዊ ሁኔታቸው።
- በእርስዎ ጉዳይ ላይ የሚመለከት ከሆነ በአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ እንዲኖሩ ስለፈቀዱልዎ ሰነዶች ዝርዝሮች።
- በአውሮፓ ህብረት+ አገር ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ እንደተማሩ የሚያሳዩ ሰነዶች ላይ ያለ መረጃ።
- ወደዚህ አገር ለመድረስ ስለተጓዙባቸው አገሮች መረጃ።
- የእርስዎ የግል ሁኔታዎች።
- የማንኛውም ቀደምት ዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎች ቀን እና የነዚያ ማመልከቻዎች ውጤት።

## ከግል መረጃዎ ጋር በተያያዘ ያሉዎት መብቶችዎ ምንድናቸው?

ለባለሥልጣናት ያቀረቡትን ማንኛውንም መረጃ የማግኘት መብት አለዎት።

ማንኛቸውም የግል መረጃዎችዎ ትክክል አይደሉም ወይም በሕጋዊ መንገድ እየተሰሩ አይደለም ብለው ካመኑ፣ ትክክል ያልሆነ መረጃ እንዲስተካከል ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ የተሰራ መረጃ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የመረጃ ተቆጣጣሪውን በማግኘት የግል መረጃዎን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ።

በዚህ አገር ያለውን የመረጃ ተቆጣጣሪ ከዚህ በታች ያለውን መረጃ በመጠቀም ማግኘት ይችላሉ።

International Protection Office, Immigration Service Delivery, 79-83 Lower Mount Street, Dublin 2, D02 ND99 or contact@ipo.gov.ie

An Roinn Dlí agus Cirt,
Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice,
Home Affairs and Migration

ይህ በራሪ ወረቀት ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደው ለኢ.ዩ. አባል ሀገራት ብቻ ነው። የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ በራሪ ጽሑፍ ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይቀበልም። በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025